# የአሜሪካና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመሳሳይነትና ተለያይነት ከታሪክ አንጻር ሲታይ

ጌታቸው ኃይሌ

## መግቢያ፤

አሜሪካና ኢትዮጵያ የሚመሳሰሉትና የሚለያዩት በብዙ ረገድ ሲሆን፥ በዚህ ጽሑፍ ላተኩር የፈለግሁት ከረገዶቹ በአንዲቷ ላይ ይሆንና፥ ድርሰቴን ከአሜሪካ የፖለቲካ ሥርዓት ልንማረው በሚገባ እደመድማለሁ። ልጽፍ የተነሣሁት፥ ኢትዮጵያን "አፍርሷት፥ አፍርሷት እስከመሠረቷ" እያሉ በመሠረቷ ላይ ለዘመቱ ጠላቶቿ "እመሰ ረሳዕኩኪ ኢትዮጵያ ለትርስዐኒ የማንየ" (መዝሙር 136፡ "ረስቸሽ እንደሆን ቀኘ እጄ ትርሳኝ") የሚል ድምፅ እንዳሰማ ግዴታ ገፋፍቶኝ ነው። (ከማህላችን የዘነጋ ሰው ካለ፥ ንጉሠ ነገሥቱና አጃቢዎቻቸው በፋሺስት ወረራ ምክንያት እንደኛ ስደተኞች በነበሩባቸውአምስት የጭንቅ ዓመታት ይህን መዝሙር ነበር በጸሎታቸው ጊዜ የሚዘምሩት።) ጠላት ሊያፈርሰውየተነሣው የኢትዮጵያ መንግሥት የተመሠረተው ከምን ላይ ነው?

አሜሪካና ኢትዮጵያ በመንግሥት አመሠራረት ላይ በዘመናት ይለያያሉ። አሜሪካ ከአዲሱ ዓለም ስትሆንኢትዮጵያ ከአሮጌው፥ ከጥንቱ ዓለም ነች። የአሜሪካ መንግሥት ከተቋቋመ ሁለት መቶ ዓመት የሞላውበቅርብ ጊዜ ነው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ዕድሜ ግን ከሦስት ሺ ዓመት ከአለፈው ብዙ ዓመታትተቈጥረዋል። ይህ ዋጋ ቢሰጠውም ባይሰጠውም፥ መሠረታዊ ልዩነት ነው።

## የአሜሪካ መንግሥት፤

አሜሪካና ኢትዮጵያ የሚመሳሰሉት የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦችን አሰባስቦ አንድ መንግሥት በማቋቋም ነው። የሚመሳሰሉትም ከታሪካቸው ከመድረሻው እንጂ ከመነሻው አይደለም። የአሜሪካ መንግሥት መነሻ መሠረቱ እንግሊዝኛ ተናጋሪውና ባህሉ ሲሆን፥ ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ (ከፈረንሳይኛ፥ ከጀርመንኛ፥ ከእስፓንኛ፥ ከሐውሳ፥ ከዐረብኛ፥ ከኦሮምኛ፥ ወዘተ.) እየጐረፉና ነባሩን ባህል እየመጠጡ በአሜሪካ መንግሥት አባልነት የተሰባሰበ አንዱ ክፍል ሆነዋል። መጠናቸውም ትንሽ አይደለም። እንዲያውም እንግሊዝኛ የሚናገረውን መሠረታዊውን ክፍል ይበልጣሉ። አንዳንዶቹ እንደሚያስታውሱት፥ ከአውሮፓ ተሰደው አሜሪካ እንደገቡ፥ ልጆቻቸው የናት አባት ቋንቋቸውን ትተው ባህሉን ለመምጠጥ በእንግሊዝኛ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው ነበረ። ማለት፥ ከየትም ይምጣ ከየት፥ አሜሪካዊ ለመሆን ሁሉም እንግሊዝኛ ይናገራል፤ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ሆኗል።

እነዚህ ስደተኞች እንግሊዝኛ የተማሩት፥ የአሜሪካን መንግሥት አባላት (አሜሪካኖች) ለመሆን እንጂ፥ እንግሊዞች ለመሆን አይደለም። እስፓንኛ ተናጋሪዎች ቍጥራቸው ትልቅ ስለሆነ፥ የአሜሪካ መንግሥት አባላት ሆነው፥ በፍላጎት የራሳቸውን ቋንቋ ለመጠበቅ ችለዋል። ሆኖም፥ ሁሉም የመንግሥቱ መሠረት የሆነውን እንግሊዝኛ ይችላሉ።

ለማጠቃለል፥ አሜሪካ በእንግሊዝ ባህል (በተለይ ቋንቋ) የተመሠረተችና ከብዙ ቋንቋዎች የመጡ ሕዝቦች እንግሊዝኛ እየተማሩ የመንግሥቱ አካል የሆኑባት አገር ነች። በሌላ አነጋገር፥ አሜሪካ በእንግሊዝኛ ባቋቋመችው መንግሥት ላይ የልዩ ልዩ ነገድ ስደተኞች (Immigrants) የሰፈሩባት አገር ነች።

## ኢትዮጵያስ?

የአሜሪካ መንግሥት መሠረቱ እንግሊዝኛ እንደሆነ ሁሉ፥ እኛ የደረስንበት የኢትዮጵያ መንግሥት መሠረቱ አማርኛ ነው። ("እኛ የደረስንበት" ስል፥ መንሥኤውን የአግዓዝያንን፥ ከዚያም የዛጔን መንግሥት በማሰብ ነው።) ኢትዮጵያ ግን የአማርኛ መንግሥት ያቋቋመችው እተለያዩ ነገዶችና ጎሳዎች ላይ ነው። ቀጥሎ፥ የተለያየ ቋንቋ ከሚናገሩ ነገዶችና ጎሳዎች የሚወለዱ ኢትዮጵያውያን የመንግሥቱ አባል ለመሆን አስፈልጓቸው አማርኛ ይማራሉ። አማርኛ ስለተማሩ አማራ ሆኑ ወይስ አማራም የአማራው መንግሥት አካልም ሆኑ? ወይስ ነገዳቸውን ይዘው የአማራው መንግሥት አካል ብቻ ሆኑ? እንደሚመስለኝ፥ ሁለቱም ወገኖች አሉን፤ ነገዳቸውን ያልለቀቁ አማርኛ ተናጋሪዎች አሉ። ነገዳቸውን ለቅቀው አማራም፥ የአማራው መንግሥት አካልም የሆኑ አሉ።

በቋንቋ መንፏቀቅ ምንም ዓይነት ትርጉም ቢሰጠው፥ ዛሬ አማርኛ የምንናገርና አማራ ነን የምንል የብዙዎቻችን ጥንት አማራ አይደለም። "አማራ እየገፋ፥ አገው እየጠፋ" የሚለው አነጋገር ምስጢሩ የአገው ጎሳዎች አማራ እየሆኑ ሄዱ ማለት ነው። ከአንድ ነገድ አንድ ሰው ሲጠመቅ ነገዱን ትቶ ክርስቲያንም አማራም እንደሚሆን ብዙ የሰነድ ማስረጃ አለ። ለምሳሌ፥ ከዚህ በታች ከግዕዝ ምንጭ (ከገድለ አባ አካለ ክርስቶስ) የተረጐምኩት እንጒርጒሮ የአንድ ኦሮሞ ወይም አገው መንደር ሰዎች ቃል መሆን አለበት፤

> በዚያን ጊዜ አራ ጐንጐራ በምትባል አገር የሚኖሩ ወታደሮች የየአንገታቸውን ማተብ ፈትተው፥ በየጦራቸው ላይ እያሰሩ ወደ ብፁዓዊ አቡነ አካለ ክርስቶስ መጡና እንዲህ አሉት፤ "አባ ሆይ፥ በፊት አረማውያን ነበርን፤ ሕዝበ ክርስቲያኑን እናጠቃ፥ ቤተ ክርስቲያን እናቃጥል ነበር። አሁን ግን በእግዚአብሔር ምሕረት መንፈሳዊት ጥምቀትን አገኘናት። ከሕዝበ ክርስቲያኑም ጋር አንድ ሆንን። በክርስቲያን ሕግም ከነሱ ጋራ ተባበርን፤ ቤተ ክርስቲያንን ወደድናት። በማቃጠል ፈንታ ወደሷ ሄደን ድንጋይ፥ ዕንጨት፥ ውሀ ፥ ጪቃ በመሸከም በግምባታዋ ላይ ዳከርን። ከዚህ ሁሉ በኋላ አሁንም እነሆ ከሀገራችን ያሰድዱናል።

(አባ አካለ ክርስቶስ ገላውዴዎስ የሚባል የአፄ ፋሲለደስ ወንድም ልጅ ናቸው። ንጉሡ በሥልጣን ሽኩቻ አባታቸውን ሲያስገድለው፥ ሸሽተው ደብረ ሊባኖስ መነኮሱ፤ ጎንደር ተመልሰው፥ እንፍራዝ አጠገብ ዞጋ የምትባል ገዳም አቋቁመው ትልቅ ባሕታዊ ወጣቸው።)

መሠረቱን አማርኛ ያደረገ መንግሥት ሲቋቋም በውስጡ አማርኛ ቋንቋቸው ያልሆነ ጎሳዎች ነበሩ። ብዙዎቹ አማራ ሆኑ። ቀጥሎ፥ በዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት ላይ መሠረቱን አማርኛ ባደረገው መንግሥት በረይቱማና ቦረን የሚባሉ ሁለት የኦሮሞ ነገዶች ሰፈሩበት። ብዙዎች እየተጠመቁ አማራና የአማራው መንግሥት አካል ሆኑ። የአማራውን ቊጥር አተለቁት።ታላላቅ መምህራንም ወጣባቸው። ክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ስለ ትምህርት ጓደኛቸው ስለ ወልደ ጊዮርጊስ የሚሉትን እንስማ፤

> ይህ ልጅ ትውልዱ ኦሮሞ፣ አገሩ አድአ ነው። አባቱ የርእሰ ደብር ዳኜ ጭሰኛ የነበረ ሰው ነው። ወልደ ጊዮርጊስ ገና ሕፃን ሳለ በፈንጣጣ በሽታ ዓይኑን ስለታወረ አባቱ ወደ እንጦጦ አምጥቶ እባክዎ ያስተምሩልኝ ብሎ ለርእሰ ደብር ዳኜ ጥሎላቸው ሄደ። እሳቸውም መጀመሪያ ወደ ንባብ ተማሪ ቤት ቀጥሎም ወደ ዜማና ወደ ቅኔ ተማሪ ቤት እያስገቡ እንዲማር አደረጉት። ቅኔውን ከአለቃ ብርሃኑ ዘንድ ተምሮ ከተቀኘ በኋላ፣ ሐዲስ ለመማር ከየኔታ ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ ገባ። አሁን ከቅኔ አስተማሪው ከአለቃ ብርሃኑ ጋር የትምህርት ጓደኛ ሆኖ ሐዲስ ይማር ጀመር። የዚህ ልጅ አእምሮው እጅግ ብሩህ ስለሆነ ትምህርት አልመክትህ አለው። እንዲሁም የሐዲሱን ንባብ ከሥር እስከ ጫፍ በቃሉ ይዞት

ነበር። አንዱን ጉባኤ አንድ ጊዜ ብቻ ሰምቶ እስከ መያዝ ድረስ አስደናቂ የማጥናት ችሎታ ነበረው። በይበልጥ የሚያስገርመኝ ያጠናውን አለመግደፉ ነበር። የኔታ ወልደ ጊዮርጊስም በወምበሬ የሚተካ ደቀ መዝሙር አገኘሁ ብለው ደስ ስላላቸው ጀማሪዎቹን ደቀ መዛሙርት እንዲያስተምር ፈቀዱለትና ከእሳቸው ጋር በቤታቸው እንዲቀመጥ አደረጉት። . . .

በግንቦት ወር የተስቦ በሽታ በዚያ ሰፈር መግባቱን ሰማንና ሥጋት አደረብን። ቀጥሎም ዕውር ወልደ ጊዮርጊስ በተስቦ በሽታ ታሞ ተኛ። በዚህ ጊዜ የኔታ ጉባኤውን አቆሙና በሽታው እስኪያልፍ ድረስ አትምጡ ብለው መለሱን። እርሳቸው ግን ዕውር ወልደ ጊዮርጊስን በቤታቸው አስተኝተው ያስታምሙት ጀመር። ሕመሙ እየጸናበት ሄዶ ቅዠት መቃዠት ጀመረ። እርሳቸው እንደነገሩን በቅዠቱ ላይ "ምንተ ያሰልጥ ደምየ ለእመ ወረድኩ ውስተ ሙስና፤ መሬትኑ የአምነከ ወይነግር ጽድቀከ" (ተቀብሬ ብበላሽ፥ ደሜ ምን ዋጋ ይኖረዋል? መሬት አምኖህ እውነተኛነትህን ይናገራልን?) እያለ ይለፈልፍ ነበር። በዚህ አኳኋን ሕመሙ ጸንቶበት አምስት ቀን ያህል እንደታመመ ታላቁ ሰው ወልደ ጊዮርጊስ ሞተ።

## የወልደ ጊዮርጊሶች መንግሥት፤

ወልደ ጊዮርጊስ በአጭር መቀጨት ያሳዝናል። በሱ ሞት ሀገሪቱ ትልቅ ሰው አጥታለች። ግን ደራሲው ብላታ መርስዔ ኀዘን ባይነግሩን ኖሮ የሊቁ የወልደ ጊዮርጊስ ነገድ የቱ እንደሆነ አናውቅም ነበር። ያላንዳች መጠራጠር የምናውቀው መሠረቱን አማርኛ ያደረገ መንግሥት አባል መሆኑን ብቻ ነው። ታሪካችን ይኸ ነው። ስንት ወልደ ጊዮርጊሶች ከኦሮሞ፥ ከጉራጌ፥ ከወላይታ፥ ወዘተ. እየመጡ መሠረቱን አማርኛ ያደረገ መንግሥት አባላት ሆነዋል!! በአስተማሪነት ለረጅም ዘመን እየኖሩ ታላላቅ ሊቃውንት ካፈሩት መምህራን ውስጥ ብዙ ወልደ ጊዮርጊሶች ነበሩን። ዛሬ ነውኮ "ብሔሩ፥ ብሔረ ሰቡ ከየት ነው?" እያልን በኢትዮጵያዊነት ታሪክ ሠርተው፥ ኮርተውና አኩርተውን ባለፉት እናት አባቶቻችን ላይ የማያውቁትን ዘርኝነት መለጠፍ ያመጣነው! ያም ቢሆን፥ የማይቻል ሙከራ ነው። ማወቂያ የለውም። ባለፈው ዘመን የኖሩ ወልደ ጊዮርጊስ፥ ዕንባቆም፥ መንግሥቱ፥ ገብረ ማርያም፥ ወለተ ማርያም፥ ካሣ፥ ግርማ፥ ጌታቸው ከየትኛው ነገድ ናቸው? ታሪክ እንደሆን ለነገድ ዋጋ ሰጥቶ አልመዘገበውም። የመንግሥቱ መሠረት የነወልደ ጊዮርጊስ ባህል (ቋንቋና ሃይማኖት) ነበረ።

አማርኛ የአማሮች ብቻ መሆኑ ቀርቶ የሌሎችም (የዶርዜዎች፥ የወላይታዎች፥ የአዳሎች፥ የኦሮሞዎች፥ ወዘተ.) ቋንቋ እየሆነ ስለሄደ፥ ሴማዊ መልኩ እየተለወጠ ሄዷል። ቋንቋው የሁሉም ሆኗል። ይህም ማለት ኢትዮጵያውያንን በባህል (በቋንቋ) አንድ ሕዝብ አድርጓቸዋል ማለት ነው። ሂደቱም የተፈጥሮ እንጂ የሰው (የመንግሥት) እጅ ገብቶበት አይደለም።

አማርኛ የተስፋፋው "ተፈጥሮያዊ መንገድን ተከትሎ ነው" ያልኩትን አንዳንድ ሰዎች ሊያስተባብሉ ሞክረዋል። ግን ታሪካችን የመዘገበውን የማያውቁ ቢሆኑ ነው። የትኛው ሕግ ነው አጼ ዮሐንስንና የትግራይን ሹማምንት በአማርኛ እንዲሠሩ ያስገደዳቸው? ኤርትራ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት በነበረችበት ጊዜ እንኳን አማርኛ ይሰጥባቸው የነበሩ ትምህርት ቤቶች ነበሩ። በዓሥራ ስድስተኛው መቶ ዓመት ግራኝ ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ለወታደሮቹ የሰጠው የጦር ዘዴ ምክር፥ በጭለማ ከሕዝብ ማህል ሲገቡ አዳሎች መሆናቸው እንዳይታወቅ በክርስቲያንኛ (በአማርኛ) ቋንቋ እንዲናገሩ ነበር። በጭለማው ማህል አንድ ሰው "ማነህ?" ሲል፥ ግራኝ፥ "እኛ ነን" የሚል መልስ ሰጠ። በዚህ የተዘናጋውን ክርስቲያን በሳንጃ ዘከዘኩት። የትኛው ሕግ አስገድዷቸው የተማሩትን አማርኛ ነው የተጠወሙበት? በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የመንግሥቱ ቋንቋ አማርኛ እንዲሆን

መደንገጉን ከሆነ፥ ያለፈን ድርጊት ወደፊት በሚሆን ድርጊት ማስመስከር ይሆናል። የተደነገገው አማርኛ ከተስፋፋ በኋላ የሆነውን አጻና እንጂ፥ እንዲስፋፋ አላደረገውም።

አዎን፥ አማርኛ በትምህርት ቤት የማስተማር ችሎታ በሌላቸው አስተማሪዎች ይሰጥ ነበረ። ታዲያ፥ እንግሊዝኛ ማስተማር የማይችል አስተማሪ ቢበድል፥ እንግሊዝኛን የሚጠላ ይኖራል? ደሞስ መንግሥት የሚሠራበት ቋንቋ በተፈጥሮ በተስፋፋው በአማርኛ ከሆነ፥ መሥሪያውን ቋንቋ ለሠራተኛው ማስተማር የሚጠበቅ አይደለም እንዴ!! አማርኛ የማያውቁ የአማርኛ ትምህርት ባይሰጣቸው ኖሮ፥ ክሱ እኮ የባሰና ለእውነት የቀረበ ይሆን ነበር፤ ክሱ፥ “በመንግሥቱ አስተዳደር ከአማሮች በቀር ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳይካፈል አማርኛ እንዳንማር ያደርጉ ነበር” የሚል ይሆን ነበር።

ስለብሔራዊ ቋንቋ ስንወያይ፥ ኦሮምኛ የአማርኛን ቦታ ይወስደዋል ብሎ የሰጋ ሰው አላየሁም። ካለም ምክሬ አይስጋ ነው። ሁሉም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ናቸው። ውሳኔው የሕዝብ ከሆነ፥ የሕዝብ ውሳኔ ማክበር ግዴታችንና ደስታችን ነው። “ኦሮሞዎች ኦሮምኛን በኢትዮጵያ ፊደል ካልተማሩ” ብዬም አላውቅም። ያልኩትን መድገም ካስፈለገ፥ በፈለጉት ፊደል ይጻፉት። ግን ከብዙዎቹ ቋንቋዎች ማህል በበቂ ምክንያት ተመርጦ፥ ተጨማሪ ብሔራዊ ቋንቋ እንዲሆን ከተፈለገ፥ በአገራችን ፊደል እንማረው። ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲማሩት የሚሰጠው ምክንያት ኦሮምኛ ከሚነገርበት አካባቢ ለንግድ ይጠቅማል ከሆነ፥ አርኪ ምክንያት አይደለምና እዚያ ሄዶ የማይነግደውን አናስገድደው። ካስገደድነው፥ ስለማይሠራበት ከትምህርት ቤት እንደወጣ ይረሳዋል።

ስለ ቋንቋ ስንተች፥ ማስተወስ ያለብን፥ ዛሬ የነገድ ስም እንደ መኪና ወይም እንደ ሌላ ምርት ስም (brand name) መሆኑን ነው። ለምሳሌ፥ የኔ መኪና ሆንዳ ነች። ሆንዳ ስሟ ነው እንጂ ንብረትነቷ የሚስተር ሆንዳ ወይም የሆንዳ ኩባንያ አይደለም። የኔ ንብረት ነች። አማርኛም የአማሮች ብቻ መሆኑ ከቀረ ዘግይቷል። የሌሎቹ ቋንቋዎች ሁኔታም እንዲሁ ሳይሆን አይቀርም። ግን ማን እንደ እንግሊዝኛ፥ እንደ ዐረቢኛ፥ እንደ አማርኛ? ቋንቋ ከነገድ ወጥቶ የግለሰብ የመሆን ጠባይ አለው። ስንጠይቅም፥ “ቋንቋህ/ሽ ምንድነው?” ብለን እንጂ፥ “የማንን ቋንቋ ነው የምትናገረው/ሪው?” ብለን አይደለም። ቋንቋን ይወርሱታል እንጂ አይዋሱትም።

# አሜሪካኖች፤

በዚህ ረገድ አሜሪካኖች ከኢትዮጵያውያን ይለያሉ። የቤተ ሰብ ስማቸውን (family name) ስለሚጠብቁ ፥ ከአውሮፓ ከየትኛው አገር እንደመጡ መገመት ይቻላል። ሆኖም፥ በእንግሊዝኛ የተመሠረተው የአሜሪካ መንግሥት አባላት መሆናቸውን ግን በኩራት ነው የሚናገሩት። ወደኢትዮጵያ ታሪክ ስንመጣ፥ በአማርኛ ላይ በተመሠረተው የኢትዮጵያ መንግሥት አባል በመሆናቸው ኩራት የማይሰማቸው ሰዎች እንዳሉ ይታወቃል። ለምን ይሆን? ሌሎች ከአውሮፓ እየመጡ ለአፍሪካውያን መንግሥት ሲፈጥሩላቸው፥ እኛ ለራሳችን መንግሥት መፍጠራችን የሚያኮራና ለፈጣሪዎቹ አባቶቻችን ሐውልት ሊቆምላቸው ሲገባ፥ ባዳ ማድረግ ከምን የመጣ ነው? አገሪቱ አማሮችና አማሮች ያልሆኑ ስለሚፎካከሩባት ይሆን? ምክንያቱ ይኸ ከሆነ፥ የጎሳ ድምበር ከተጣሰ ዘመናት አልፈዋል። ምንም ኃይል መልሶ ሊገነባው አይችልም። ከዛሬዎቹ አማሮች ብዙዎቹ እነ ወልደ ጊዮርጊስ ናቸው። ሁለተኛም፥ በዛሬይቷ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ነገዶች ሁሉ የሚኖሩት አባቶቻቸው በነበሩባትና በታሪኳ ከሞላ ጐደል በተሳተፉበት ሀገር ውስጥ ነው። ግማሾቹ (ለምሳሌ፥ የቦረንና የበረይቱማ ጎሳዎች) ለከብቶቻቸው ሣር ፍለጋ ወደማህል ኢትዮጵያ መምጣታቸውን ይዞ መጤዎች ናቸው ማለት ከዚያ በፊት የነበሩበትን አገር የኢትዮጵያ ክፍል አልነበረም ማለት ይሆናል። ጉዟቸው ከአንዱ የኢትዮጵያ ግዛት

ተነሥተው ወደሌላው ኢትዮጵያ ግዛት ነው። በርግጥ፥ ጉዟቸው ወረራ ስለነበረ ጉዳት አስከትሏል። የኢትዮጵያን መንግሥት መሠረት ግን ማንም ይጣለው ማንም፥ እግንባታው ላይ ሁሉም ስለተሳተፈ፥ በኢትዮጵያ መንግሥት መቋቋም መኰራት በአባቶቻችን አስተዋፅኦ መኰራት ነው። ሁሉም በአባቱ አስተዋፅኦ እንዲኮራ፥ ድምፃችንን እናሰማለን።

## ከአሜሪካ የምንማረው፤

የአማራው ሕዝብ፥ ታሪኩ በምንም ዓይነት እየተተነተነ ቢተረክ፥ አባሎቹም የቶቹና የቶቹ (ቀደምትና ደኅርት) ቢባሉም፥ አሁንም እንደቀድሞው ከኢትዮጵያ ነገዶች አንዱ ነው። እዚያው በኅሳቸው የቆዩቱ ኢትዮጵያውያን፥ “አማራውም እኛ ነን” አላሉም። ስለዚህ፥ ኢትዮጵያ እንደ አሜሪካ ብዙ ነገዶች ያላት አገር መሆኗን ተቀብላ፥ አገሪቱ ከአሜሪካ ፖለቲካዊ ሥርዓት የምትማረው ይኖራታል። ይኸም አንደኛ፥ የነገድ ፓርቲ አለማቋቋም ነው። የነገድ ፓርቲ ማቋቋም በመንግሥቱ ጥንታዊነት የሚኮራውንና ወደ አዲሱ ዘመን ለመግባት የሚዳክረውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በሺ ዓመት ወደ ኋላ ወደ ዘመነ ነገድ መመለስና አገሪቷን ከመበታተን አደጋ ላይ መጣል ነው። የትግራይ ወያኔዎች የሚሉት “ሕዝቡን በነገድ ያለያየነው እንዳይለያይ ነው” ነው። እውነታቸው በሆነ በማን ዕድል። ግን እነሱና መሰሎቻቸው እንዲህ አሉ እንጂ ሕዝባችን ኅሳችን አለያየን አላለም። ደግሞስ መለያየት መለያየትን እንጂ አለመለያየትን አያመጣም። የማግኒት ብረቶችን ለማላጸቅ ሆድ ለሆድ ማገናኘት እንጂ፥ ጀርባ ለጀርዳ ማገናኘትማ እንዳይላጸቁ ማድረግ ነው። የኅሳን ፖለቲካ ሕዝቡም እንዳልፈለገው ያደረጉት የብዙ ዓመታት ሙከራ ውጤት ነግሯቸዋል። ሕዝቡን በነገድ ያለያዩበት ምክንያታቸው ሌላ እንደሆነ ሁሉም ያውቀዋል።

“በሀገር አንድነት እናምናለን” የሚሉ የኦሮሞ ፖለቲከኞች ስለክልሎች መደምሰስ አስፈላጊነት ስንናገር፥ ይቃወማሉ። “ክልልን የጠላችሁት ኬላ መስሏችሁ ይሆናል” ይሉናል። በዚያ ዓይን ካነሡት፥ ክልል እውነትም ኬላ ነው። ዘበኛ ያልቆመበት ስለማይቻል ነው። የደቡብ ሱዳንና የሱማሊያ ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ የሚጎርፉት ማንም ሳያግዳቸው ኬላ እየጣሱ ነው። የመቃድሾና የሐርጌሳ ነዋሪዎች የሚገናኙት ማንም ሳይጠይቃቸው በኢትዮጵያ መሬት እያቋረጡ ነው። ኮንትሮ ባንድ ንግድ እንደተጧጧፈ ነው። አፍሪካ ውስጥ ኬላ አይሠራም። ኬላና ክልል አንድ መሆናቸውን አንጠራጠር። በክልል ድምበሮች ላይ አሁን ዘበኛ ሊቆምባቸው አይቻልም። ግን የሚቻልበት ጊዜ እንዳይመጣ የሚከለክለው የለም። እስከዚያ ማድረግ የሚቻለው “የክልሉ ዜጎች አይደላችሁም” የሚባሉትን ኢትዮጵያውያን ማባረር ወይም መግደል ነው። **በኢትዮጵያ አንድነት ለሚያምኑ ኢትዮጵያውያን ያለኝ ምክር፥ የክልል ፖለቲካን በይፋ የማይረግሙና ከራእይ ሰነዳቸው ውስጥ ያስገቡ ወገኖችን እንዳያምኑና አብረዋቸው እንዳይዶልቱ ነው። በክልል የሚያምኑ ኢትዮጵያውያን ካሉ፥ ወይ ሳይገባቸው ነገር የሚያበላሹ ወይም የጋራ ጠላት እስኪወገድ ያደፈጡ ተኵላዎች ናቸው። እሳትና ጭድ እጅ ለጅ ተያይዘው ሽር ሽር አይሄዱም።** ክልል ይደምሰስ ስንል፥ ያላልነውን፥ “ፌደራል አስተዳደር ይቅር ትላላችሁ” ይሉናል፤ **አላልንም**። አታወናብዱ። ያልነው አገሪቱ ለፌዴሬሽን አስተዳደር ስትከፋፈል መስፈርቱ ቋንቋ ወይም “ዘር” አይሁን ነው።

***ሁለተኛው*** ትምህርት ***የጥቅም ማኅበር*** ማቋቋም ነው። የአሜሪካ ጥቁሮች የጥቅም ማኅበር አላቸው። የአሜሪካ እስፓኞች የጥቅም ማኅበር አላቸው። የአሜሪካ ሴቶች፥ የአሜሪካ መምህራን፥ የአሜሪካ ሠራተኞች የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚያንበረክኩ የጥቅም ማኅበሮች አላቸው። በምርጫ ጊዜ ድምፃቸውን ለሚጠቅማቸው ተወዳዳሪ ይሰጣሉ። ኢትዮጵያውያንም በኅሳቸው፥ በነገዳቸው፥ በሃይማኖታቸው፥ በሙያቸው፥ በቀበሌያቸው፥ በታቦታቸው የጥቅም ማኅበሮች አቋቁመው፥ ጥቅማቸውን ሊተብቁና ሊያዳብሩ ይችላሉ፤ ቋንቋቸውን ያዳብራሉ፤ ሃይማኖታቸውን ያስፋፋሉ፤ በእድር ይረዳዳሉ፥ በምርጫ ጊዜ ድምፃቸውን

ለሚጠቅማቸው ተወዳዳሪ ይሰጣሉ። እነዚህን ማኅበሮች ከፖለቲካ ፓርቲ ለመለየት civic organizations ይሏቸዋል። በአማርኛ **ማኅበረ ሰባዊ ድርጅቶች** ይሏቸዋል። ወያኔዎች የሚያበረታቷቸው **የጎሳ ፓርቲዎች** ይጐዱናል፤ ይበታትኑናል። የጥቅም ማኅበሮች **(ማኅበረ ሰባዊ ድርጅቶች)** ይጠቅሙናል፤ አንድነታችንን ይጠብቁልናል። እኩልነት እንዳይዛባ፥ አድልዎ እንዳይነግሥ፥ ነፃነታችን ተከብሮ እንዲኖር ነቅተው ይጠብቃሉ። የማኅበረ ሰባዊ ድርጅቶችና የፖለቲካ ፓርቲዎች አባል መሆንን እንደ ብሔራዊ ግዴታችን እንየው።